ጎሕ
የጎንደር ሕብረት

ጁላይ 23፣ 2016

# አስቸኳይ መልዕክት ለጎንደር ህዝብ

የጎንደር ህዝብ ሆይ፤

የወያኔ የሽብር ግብረ ኃይል የከፈተብህን ወረራ ለመከላከል የፈጸምከው ተጋድሎና የከፈልከው መጽዋዕትነት፤ የጎንደርን ጀግንነት ያስመሰከረ፣ የወያኔን አሸባሪነት ያጋለጠ አብይ ምዕራፍ ነው። ጀግኖች ልጆችህ ከቆላውና ከደጋው ተሰባስበው፣ አሸባሪውን የወያኔ ግብረ ኃይል ደምስሰው፣ በታሪካዊ መዲናችን የከፈሉት የህይወት መጽዋዕትነት የጽኑ አንድነታችን ምስክር ነው። ይህ ጀግንነትና ጠንካራ አንድነት ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ኩራት ሆኗል።

ወደፊትም፤ ይህ አሸባሪ ቡድን፣ ከጥፋቱ ይማራል፣ ይቅርታ ይጠይቃል ወይም የህዝቡን ጥያቄ ይመልሳል ብለህ እንዳትታለል። ወያኔ ከአፈጣጠሩ ጀምሮ፣ አማራውን በጠላትነት ፈርጆ የተነሳ በመሆኑ፣ በህዝብ ላይ ከመዝመት አይቆጠብምና ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

በቅርቡ ከወያኔ የደህንነት ምንጮች የሚሾልኩ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤

1. የወያኔ የሽብር ግብረኃይል፣ ህዝቡን እንደፈለገ ማሰርና መግደል እንዲችል፣ የጎንደርን ህዝብ ትጥቅ ለማስፈታት፣
2. ለአማራ ህዝብ ይቆረቆራሉ የሚባሉ ባለስልጣኖችን በተለያዩ ወንጀሎች አሳብቦ ማሰርና በህዝብ ማስጠላት፣
3. አማራ የሆኑ የፖሊስና የሚሊሺያ መሪዎችን በማባረር በምትካቸው ጸረ አማራ ተላላኪዎቹን ለመሾም፣
4. የወልቃይትን የማንነት ጥያቄ ይደግፋሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ተማሪዎችና የህዝብ ተቆርቋሪዎችን ለማሰር መዘጋጀቱን ይጠቁማሉ።

በመሆኑ፣ ይህችን አስቸኳይ መልዕክት ማስተላለፍ እንወዳለን፤

- ሁሉም ወገናችን ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርግና ይህን መልዕክት ለሌሎች እንድናስተላልፍ፣
- ማንም ሰው ለወያኔ ትጥቁን እንዳይፈታ ማስተባበር፣
- ማንም ሰው ከወያኔ ጋር እንዳይተባበር፣
- ማንም ሰው ወገኑን ለወያኔ አሳልፎ እንዳይሰጥ፣
- ማንም ሰው ከወያኔ እጅ ቢወድቅ፣ ሚስጢር ሰጥቶ ወገኑን እንዳይጎዳ፣
- ማንም ሰው በወገኑ ላይ መስክሮ የወያኔ መሳሪያ እንዳይሆን፣
- ማንም ሰው በወያኔ ቢታሰር፣ በአስቸኳይ በማን እንደተያዙ፣ የት እንደሚገኙ ለህዝብ ማስታወቅ፣
- ወያኔ በስውር ህዝብ ማጥቃቱ ከጀመረ በጥሩምባ ወይም በፊሽካ ህዝብ እንዲያውቀው ማድረግ፣

እነዚህንና ሌሎችንም ዝግጅቶች በማድረግ፣ በቅርቡ የታየውን የጀግንነት ተጋድሎ እንደገና መደገም ይቻላል።